| | |
|---|---|
| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ<br>ኢየሱስ ክርስቶስ<br>ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ<br>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር<br>ድንግል ማርያም<br>እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ<br>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ |
| **The Triumphant Lion of the Tribe of Judah**<br>**Jesus Christ**<br>**Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian**<br>**King of Zion and King of Kings of Ethiopia** | **Ethiopia stretches out Her Hands to God**<br>**The Virgin Mary**<br>**Mother of God and Our Holy Mother**<br>**Queen of Zion and Ethiopia** |

ቍጥር ፰/፳፻፯ ዓ. ም.

# ቃለ ዐዋዲ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የአዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤
አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥
ወንግሥትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥
ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።

ማለትም፦

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እናታችንና ሃይማኖታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን
በኾነችው፡ አምላክን በወለደችው፡
በእመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በአምላክነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና
የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ በኾነው፡
አባታችንና መድኃኒታችን፥ ካህናችንና ንጉሣችን
ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ \+ \+

በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥ በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥ በሕይወቴ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፡ ለዓለሙ ሰዎች ኹሉ፡ ለወንዶቼም፡ ለሴቶቼም!

ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡ የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡ በስሜ፡ ተጠርታችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፡ ለወንዶቼ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ለሴቶቼ ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ በሙሉ!

በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራው፥ እናቱና መቅደሱ ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ጸጋዬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!

## መግቢያ

እንዳለፈው፡ እንደ፯ተኛው የአዋጅ ቃሌ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመቤታችሁና ምድረ ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እርሷም፡ እኔ ድንግል ማርያም ነኝ።**

ካለፈው አቻምና፡ ከነሓሴ ፲፯ ቀን፥ ፳፻፫ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ፡ በቅድሚያ፡ በልጄ በወዳጄ፡ በኢየሱስ መሢሕ፥ ከዚያም ተከታትሎ፡ በእኔ፡ በእናቱ፡ በድንግል ማርያም በኩል፡ በተነገሩት የአዋጅ ቃሎቻችን አማካይነት፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያን፡** የህልውና ዝክረ ነገር በሚመለከት፡ መለኮታዊ እውነታውን፡ በይበልጥ፡ ለእናንተ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ልጆቻችን ብቻ ሳይኾን፡ ለቀረው ፍጥረታችን ኹሉ፡ በይፋ በመግለጥ፡ በየጊዜያቱ፡ የቃለ ዐዋዲ መልእክቶቻችንን ስናስተላልፍላችሁ እንደቆየን ታስታውሳላችሁ።

አኹን፡ እነዚያን የአዋጅ ቃሎቻችንን በመከተል፡ ከእነዚያ ጊዜያት አንሥቶ፡-

፩ደኛ፡- በግእዙና በኢትዮጵያኛው፥ በእንግሊዝኛውም ቋንቋ የምታሰሙት የዘወትሩ የሃይማኖት ጸሎታችሁ፡ ከዚህ በታች፡ እንደሚከተለው ተሟልቶ ስለቀረበላችሁ፡ በቀደመው ቦታ፡ ይህን የተሟላውን፡ አዲሱን ተክታችሁ፥ ተጠሪዎች ካህናት ልጆቼም፡ በየጎዋ ሰሌዳዎቻችሁና መድረኮቻችሁ ላይ ሳይቀር አሥፍራችሁ፥ ለሌሎቻችሁም ኹሉ፡ ይኸው ዜና ተላልፎላችሁ፡ እንድታውቁት በማድረግ፡ ኹላችሁም፡ እንድትጠቀሙበት ይኹን!

## ጸሎተ ሃይማኖት፡
## ዘኢትዮጵያውያን ወዘኢትዮጵያውያት።

### ንሕነ ኢትዮጵያውያን፥ ወኢትዮጵያውያት፡-

ነአምን፡ በአሓዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር አብወእም፡ አኀዜ ኵሉ፥ ገባሬ ሰማያት ወምድር፡ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ።

ወነአምን፡ በትሥልስተ አሓዱ አምላክ፡ ዘግህደ በተዋሕዶ ህላዌሃ፥ ወበአካላ ለድንግል ማርያም፡ እንተ ይእቲ፡ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፥ ወኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር።

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አሐዱ እግዚእ፥ ወልድ ዋሕድ፡ እምእግዚአብሔር አብወእም፥ ዘህልው ምስሌሁ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ብርሃን፡ ዘእምብርሃን፥ አምላክ፡ ዘእምአምላክ፡ ዘበአማን፤ ዘተወልደ፡ ወአኮ ዘተገብረ፥ ዘዕሩይ ምስለ አብወእም፡ በመለኮቱ፤ ዘቦቱ፡ ኵሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ፡ አልቦ ዘኮነ፥ ወኢምንትኒ፥ ዘበሰማይኒ፥ ወዘበምድርኒ። ዘበእንቲአነ ለሰብእ፥ ወበእንተ መድኃኒትነ፡ ወረደ እምሰማያት፤ ተሰብአ፤ ወተሠገወ፤ ወኮነ፡ ብእሴ ፍጹመ፡ በነሢአ ሥጋ፡ እምሥጋሃ፥ ወነፍስ፡ እምነፍሳ፡ እምማርያም፡ እምቅድስት ድንግል፡ ዘተዋሓደት እግዚአብሔር አብወእም፡ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ዘበቅድም። በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፡ ተሰቅለ፤ ወሓመ፥ ወሞተ፤ ወተቀብረ በእንቲአነ። ወተንሥአ እሙታን፡ አመ ሣልስት ዕለት። ዐርገ በስብሓት፡ ውስተ ሰማያት። ወነበረ፡ በየማነ አቡሁወእሙ፥ በመንበሩ ዘበዕሪና። ዳግመ ይመጽእ በስብሓት፤ ይኰንን፡ ሕያዋነ፥ ወሙታነ። ወአልባቲ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፡ ዘተሰምየት፡ "ኢትዮጵያ"።

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ። ውእቱ መንፈሰ ጽድቅ፥ ማኅየዊ ዘበአማን፥ ዘሠረፀ እምእግዚአብሔር አብወእም፥ ዘንሰግድ ሎቱ፥ ወንሰብሖ፡ ምስለ አብወእም፥ ወወልድ፥ ወዘነበበ በነቢያት፥ ዘወረደ ላዕለ ሓዋርያት፥ ወጸጋሁ፡ ዘመልዓ ዓለመ፡ በቤዛ መስቀሉ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ።

ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ይእቲ፡ ዘመሠረታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እምጥንት፡ በኪዳነ ልቦና፡ ዘሰብኣውያን ቀደምት፥ ወዘአጽንዓት፡ በቃለ ነቢያት፥ ወዘፈጸማ፡ በላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሓዋርያት። በውስቴታ፡ ያቄርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወባቲ ይትዌከፉ ምእመናን፥ ወምእመናት፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሁ።

ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት፡ ለስርየተ ኃጢአት።

ወነአምን፡ በትንሣኤ ሙታን፤ ወሕይወት፡ ዘለዓለም። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

# *የሃይማኖት ጸሎት፡*
# *የኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያውያት።*

## እኛ ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት፡-

ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብወእም እናምናለን።

መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በድንግል ማርያም፡ የተዋሕዶ አኗኗርና አካል በተገለጠው፡ በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የእግዚአብሔር አብወእም ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ፡ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከአብወእም ጋራ የሚተካከል፥ ኹሉ፡ በእርሱ የኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፥ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ግብር፡ እግዚአብሔር አብወእም ከተዋሓዱት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፥ ከነፍሷም፡ ነፍስን ነሥቶ፡ ፍጹም ሰውን ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱና እናቱም ቀኝ፡ በእኩያ ዙፋኑ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። "ኢትዮጵያ" ለተባለችው መንግሥቱም፡ ፍጻሜ የላትም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከእግዚአብሔር አብወእም የሠረፀና በነቢያት ዐድሮ የተናገረው፥ በሓዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ፡ የመስቀሉ ቤዛነት፡ ዓለሙን፡ በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። ለእርሱም፡ ከአብወእም እና ከወልድ ጋር እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለንም።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጥንት፡ በቀደሙት ሰዎች ኪዳነ ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሓዋርያት ጉባኤ በፈጸማት፥ ካህናት፡ የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚያቀርቡባት፥ ምእመናንና ምእመናትም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋዎች በሚቀበሉባት፡ በአንዲት ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እናምናለን።

ኃጢኣት በሚሰረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

በሙታን ትንሣኤ፥ በዘለዓለምም ሕይወት እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

# THE ETHIOPIAN CREED

We Ethiopians believe in One God, The Father and Mother, Almighty who possesses all, Maker of the Heavens and Earth, the visible and the invisible.

We believe in God The Holy Trinity embodied in The Co-existent and Incarnate Divine Person of The Virgin Mary, Ethiopia: The Kingdom of God.

We believe in God The Son, Jesus Christ, One Lord, the only begotten Son of God The Father and Mother, who was with Him before the creation of the world. He is Light from Light, True God from True God, begotten not made, and, in His Divine Essence, one with His Father and Mother. All things were made by Him, and without Him nothing whatsoever was made, in Heavens or on Earth.

He came down from Heavens for our sake, for the sake of humanity, for our salvation. He was Incarnate in the womb of The Virgin Mary with Whom God The Father and Mother is united by the preceding Divine Work of The Holy Spirit, and, acquiring the human soul and the human flesh from Her, became the Perfect Man.

In the days of Pontius Pilate, He suffered, was crucified, died and was buried for our sake. And He rose from the dead on the third day, ascended in glory into Heavens and sat on His Throne at the right-hand of His Father and Mother.

He will come again in glory to judge the living and the dead. There is no end to His Kingdom, ever identified as "Ethiopia".

We believe in God The Holy Spirit. He is the True and the life-giving Spirit who proceeds from God The Father and Mother, spoke through the Prophets, and, by the atonement of Jesus Christ, descended upon the Apostles and filled the world with His Grace. We worship and glorify Him with God The Father and Mother and God The Son.

We believe in the One Holy Ethiopia: The Kingdom of God that was founded by the Divine Incarnate Word, Jesus Christ, initially in the Hearts of the Patriarchs and Matriarchs, and later sustained by His Divine Messages through the Prophets, and finally brought to perfection through the Holy Spirit by His convocation of the Apostles, and where priests offer His Holy Body and Sacred Blood as Sacrifice for the Holy Communion with God, and where the Sacramental Blessings of the Holy Spirit are bestowed upon and communicated to all believers.

We believe in One Baptism for the remission of sins.

We believe in the Resurrection from the dead and the Life in Eternity, world without end. Amen.

፪ተኛ፡-

*"ኢትዮጵያ ሆይ፥ ሀገራችን! ረስቼሽ እንደኾን፡ ቀኜ ትርሳኝ፤*
*ያላሰብሁሽ እንደኾን፡ መላሴ፡ ትናጋዬን፡ ሰልቶ ይውጋኝ፤*
*ከደስታዬ ኹሉ በላይ፡ ኢትዮጵያ ሆይ! አንቺ ባትኾኝ ስደት ይብላኝ።*
*አቤቱ፥ ፈጣሪያችን! በኢትዮጵያ ቀን፡ ጠላቶቿን ኹሉ አስብ፤*
*'አፍርሷት፡ ኢትዮጵያን፡ እስከመሠረቷ ድረስ!' የሚሉትንም ሕዝብ።*
*እናንት ትምክህተኞች፡ የኢትዮጵያ ፀሮች! የተንኰላችሁን ብድራት፤*
*የሚመልስ ነው፡ አምላካችን፡ በፍትሕ፥ በተአምራት፤*
*በሚጠሉሽ ላይ፡ በእውነት፥*
*በቅን ለሚፈርደው ንጉሥ፡ ምስጋናችን ይብዛለት።*
*ኢትዮጵያ ሆይ፥ ሀገራችን! ረስቼሽ እንደኾነ፡ ቀኜ ትርሳኝ።"*

የሚለውን፡ "የመከራ ጊዜ መዝሙራችን" ያላችሁትንና ስደትን የሚያካትተውን፡ የዜማ ጸሎታችሁን፡ እንግዴህ ወዲህ፡ በፊታችን አትዘምሩትም።

ምክንያቱን፡ ባጭሩ ልግለጥላችሁ፡-

ጥንቱንም ቢኾን፡ የእኔ፡ የኢትዮጵያ ልጆቼ በኾናችሁት፡ በእናንተ ዘንድ፡ <u>ፍልሰት</u> እንጂ፡ ምንም ዓይነት ስደት፡ ፈጽሞ የለባችሁም።

"ኢትዮጵያ" ተብላ፡ በስሜ ከምትጠራው ምድረ ገነት እየተነሣችሁ፡ ወደዓለሙ የምድር ስፋቷ ኹሉ በመጓዝና በመሥፈር ስታካኺዱ የኖራችሁትን፡ ይህንኑ ፍልሰታችሁን የጀመራችሁት፡ ገና፡ በወላጆቻችሁ፡ በአዳምና በሔዋን የልደት ዘመን ነው።

ይኸውም፡ ጌታዬ እግዚአብሔር፡ ወንድና ሴት አድርጎ፡ በእኛ አርአያና ሥርዓት የፈጠራቸውን፡ እኒያን የዘር ግንዳችሁን፡ ከባረክናቸው በኋላ፡ **"ብዝኁ! ወተባዝኁ! ወምልእዋ ለምድር! ወቅንይዋ! ወኰንንዎሙ፡ ለዓሣተ ባሕር፥ ወለአራዊተ ምድር፥ ወለአዕዋፈ ሰማይ፥ ወለኵሉ እንስሳ፥ ወለኵሉ ዘይትሓወስ ዲበ ምድር!"**

**"ብዙ! ተባዙ! ምድርንም ሙሏት! አልሟትም! የባሕር ዓሦችን፥ የምድር አውሬዎችንና የሰማይ ወፎችን፥ በመሬት ላይ የሚርመሰመሰውን እንስሳና ተንቀሳቃሽ ፍጥረትም ኹሉ አስተዳድሩ!"** የሚለውን መለኮታዊ መመሪያ፡ በተፈጥሮም፥ በእውቀትም አጎናፅፈናቸው ስለነበረ፡ እናንተ ትውልዶቻቸው ልጆቻችን፡ ወደዓለሙ ኹሉ የምድር ስፋቷ የጀመራችሁት፡ ያ ፍልሰታችሁ፡ በዚያ መሠረት ሲካኼድ የኖረ በመኾኑ ነው። (ዘፍጥ. ፩፥ ፳፯-፳፰።)

ከጥፋት ውኃ በፊት የታየችው፡ የኖኅና የሓይከል መርከብም፡ ከዚህችው የገነት ምድሬ፡ ከኢትዮጵያ ተነሥታ፡ ጉዞዋን፡ ወደአራራት ኮረብታ ያመራችው፡ ከዚሁ መለኮታዊ መመሪያ የተነሣ፡ በመፍለስ እንጂ፡ በስደት መልክና ይዘት አለመኾኑን፡ ልታውቁት ይገባችኋል።

ከጥፋት ውኃ በኋላ፡ ከእርሷ፡ ከመርከቢቱ ከወጡት፡ ከኖኅና ከሓይከል ልጆች ከተወለዱት የልጅ ልጆች ጋብቻ የተዋለዱት፡ የቀደሙት ልጆቻችንና ካህኖቻችን፥ ተጠሪዎቻችንና አዔዎቻችን (ሥዩመ/ሥይምተ-እግዚአብሔራችን) መልከ ጼዴቅና ሳሌም፡ የኢየሩሳሌምን ቅድስት ከተማ ቈርቍረው፡ በዚያ መኖር እንደጀመሩ፡ የምታዘክሩት እውነታ ነው።

እነርሱ፡ እንዲህ፡ በኢየሩሳሌም እየበረከቱ ሣሉ፡ ከእነርሱ ያገኘኋቸው ልጆቼ፡ ስሜ ወደተጠራባት፡ ወደዚችው፡ "ኢትዮጵያ" ወደተባለችው፡ ዐፅመ ርስታቸውና ብሔረ ሙላዳቸው (የትውልድ አገራቸው) ተመልሰው፡ በዚያ ተደላድለው መኖራቸውን ቀጠሉ፤ እየበዙም ኼዱ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ፡ ይኸው፡ እስከዛሬ ድረስ፡ በኹለቱ የተቀደሱ ምድሮቼ፡ በኢትዮጵያ እና በኢየሩሳሌም መካከል፥ ወደሌሎቹም አህጉራት የሚደረገው፡ የእናንተ፡ የልጆቼ የፍልሰት ጉዞ፡ ከዚሁ መለኮታዊ መመሪያ የተነሣ፡ በፍልሰት እንጂ፡ በስደት መልክና ይዘት አለመኾኑን፡ ልትገነዘቡት ያስፈልጋችኋል።

ስደት ግን፡ ዕድል ፋንታቸውና ጽዋ ተርታቸው ኾኖ የኖረው፥ አኹንም ያለው፡ የእስራኤል ልጆች ለኾኑት፡ ለአይሁድ እንጂ፡ ለእናንተ፡ ለኢትዮጵያ ልጆቼ አይደለም። አዎን! ከአባቶቻቸው ከአብርሃም፥ ከይስሓቅና ከያዕቆብ ጊዜ ጀምሮ፡ ወደምድረ ከነዓን ኾነ፡ ወደግብፅ፥ ወደፋርስ ባቢሎንና ወደኢትዮጵያ፥ ወደቀሩትም፡ በዓለም ላይ ወዳሉ የተለያዩ አገሮች የመሰደድ ዕጣቸው ኾኖ የኖረው፡ ለእነዚሁ፡ ለአይሁድ ብቻ ነው።

የእናንተ፡ የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ ዕድል ፋንታና ጽዋ ተርታ ኾኖ የኖረው፥ አኹንም ያለው ዕጣችሁማ፡ ከመጀመሪያው አንሥቶ፡ ስደተኞችን በመልካም እንግድነት ተቀብሎ፡ በፍቅር ማስተናገድና በሰላም መሸኘት፥ ወይም ማኖር ብቻ ነው።

ልጄ ወዳጄ፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ በዚህ ረገድ፡ "ውስተ ፍኖተ አሕዛብ፡ ኢትሑሩ! ወሀገረ ሳምር፡ ኢትባኡ! ወሑሩ ባሕቱ፡ ኀበ አባግዕ፡ ዘተኀጕላ፡ ዘቤተ እስራኤል! ...ኢተፈነውኩ፡ ዘእንበለ ኀበ አባግዕ ዘተኀጕላ፡ ዘቤተ እስራኤል።"

"ወደአሕዛብ መንገድ አትሒዱ! ወደሳምራውያንም አገር አትግቡ! ነገር ግን፡ ወደጠፉት፡ ወደእስራኤል ቤት በጎች ኺዱ! ...ወደጠፉቱ ወደእስራኤል ቤት እንጂ፡ ወደሌላ አልተላክሁም።" ሲል፡ ለደቀ መዛሙርቱና ለሓዋርያቱ፡ መመሪያ ትእዛዙን አበክሮ በሰጠበት ጊዜ፡ ይህን ቃል እንደተናገረ ታስታውሳላችሁ። (ማቴ. ፲፥ ፩-፯። ፲፭፥ ጽ፩።)

ስለዚህ፡ ይህ ቃል፡ ልጇ ወዳጇ፡ በዚያ፡ በቀዳማዊው መልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነት፡ ወደዚህ ዓለም የመጣው፡ የእርሱ፡ የዘለዓለም አባታችሁ፡ የእግዚአብሔር እና የእኔ፡ የዘለዓለም እናታችሁ፡ የኢትዮጵያ ልጆች ለኾናችሁት፡ ለእናንተ ሳይኾን፡ ለእነዚያ፡ ለጠፉቱ፡ የእስራኤል ልጆች መኾኑን፡ በሚበቃ ያረጋግጥላችኋል።

እንግዴህ፡ ስደትን ኾነ፡ ሌላውን መከራ በሚመለከት፡ በፍጡሮቻችን ሰዎች መካከል ስለሚወሳው ችግር፡ መደምደሚያው ውሳኔ፡ በዚህ፡ በእግዚአብሔሩ ቃል ላይ የተመሠረተው፡ ይህ እውነት ከኾነ፡ ልጇ ወዳጇ፡ በሕፃንነቱ ወራት፡ ከበረት ልደቱ አንሥቶ፡ እስከመቃብሩና ትንሣኤው ድረስ፡ ከእኔ ጋር የተቀበላቸው የስደትና የመስቀል መከራዎቹ ኹሉ፡ በእነርሱ፡ በእስራኤል ልጆች፡ ክፋትና ክህደት፥ ዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአታቸው ምክንያት፡ የወደቀባቸውን የስደት ኾነ ሌላ የሥቃይ ፍዳ፡ በቤዛነት ለማስወገድ ስንል የፈጸምነው እንጂ፡ እናንተ፡ የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ ስደታቸውን የሚጨምረውን፡ የእነርሱን የመሰለ፡ ጠንቀኛ በደል ኖሮባችሁ፡ ያን ቅጣታችሁን ለማስተስረይ ብለን ያቀረብነው መሥዋዕትነት አይደለም።

**እናንተማ፡ በዚህ የፍጥረተ ዓለሙ ሰፊ ምድርና ጠፈር ላይ ብቻ ሳይኾን፡ በሰማያትም ጭምር፡ በምልዓት ሰፍና፥ እነዚህኑ ዓለማት፡ በፈጣሪነትና በባለቤትነት ይዛ፡ በፍጹም መልካምነት በምታስተዳድረው፡ የእኛና የእናንተ በኾነችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ምንጊዜም፡ በፈለጋችሁበትና በወደዳችሁበት አገርና ቦታ፡ የመኖር ፍጹም ነጻነታችሁና መብታችሁ፡ በሙሉ ባለሥልጣንነት የተከበረና የጸና ስለኾነ፡ አዎን! እናንተ፡ የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ስደት ከቶ የለባችሁም።**

እናንተ ልጆቻችን፡ ያንኑ የእስራኤል ልጆች ፍዳ የኾነውን ስደት በማዘከር፥ ልክ፡ በእናንተ ላይ እንደደረሰም በመቍጠር፡ ስታካኺዱት የኖራችሁበት ልማድ፡ ባለማወቅና በስሕተት መኾኑን እንዳልተረዳችሁት አውቀንላችኋል። ይኸውም፡ የአይሁድ ኦሪታውያንና የግብፅ ኦርቶክሳውያን፡ በቅደም ተከተል ባመጡባችሁ፡ በዚያ፡ የኃጢአትና የበደል ጠንቅ፡ በድምሩ፡ ለሦስት ሺ አምስት ዓመታት ስታካኺዱት የኖራችሁት፡ ምትሓታዊ የስደት መከራ ነው። እርሱም፡ በመጀመሪያ፡ እኒያ፡ የእስራኤል ልጆች፡ ሊፈጽሙት ያልቻሉትን ኪዳነ ኦሪትን፡ እናንተ፡ ቀደም ብላችሁ፡ በእኔና በልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሢሕ የታቦተ ጽዮን ሥርዓት አማካይነት፡ በታማኟ የቃል ኪዳን አጼዩት ልጃችን በኾነችው፡ በንግሥት ማክዳና በልጇ ምኒልክ እጅ፡ በባለአደራነት ተረክባችሁ፡ በይሁዲነት ለኖራችሁባቸው፡ ለአንድ ሽህ ዓመታት ስትፈጽሙት የቆያችሁት ነው፤ ከዚያም፡ በመጨረሻ፡ በእኛ ሰው የመኾን ቤዛነታችን ባስወገድነው፥ እናንተ ግን፡ ከግብፅ ኦርቶዶክሳውያን መነኮሳት ባገኛችሁት፡ የሰው ትምህርት፡ እንዳልተወገደ አድርጋችሁ፡ በሓሰት፡ እስካኹን፡ ለኹለት ሽህ አምስት ዓመታት የቀጠላችሁበት ሥራችሁ ነው።

አኹን ግን፡ በቃ! ያን በማዘከር፡ በእናንተ በኢትዮጵያ ልጆቼ ዘንድ፡ ጥንቱኑም የሌለውን፥ ይኹን እንጂ፡ በስሕተት እንዳለ ቈጥራችሁ፡ ባለማወቅ፡ ስትዘምሩት የኖራችሁትን፡ ከላይ የተጠቀሰውን፡ የስደትና የመከራ መዝሙር፡ አዎን! እንግዴህ ወዲህ፡ አትዘምሩትም።

፫ተኛ፡- የእኔን፡ የእናታችሁን መለኮታዊና ትስብእታዊ ማንነት በሚመለከት፡ እስካኹን እየተብራራ ሲገለጽላችሁ የቆየውን፡ የእግዚአብሔር እውነት የሚያጠናክር ምስክር፡ ይኸው በድጋሚ፡ እንደሚከተለው፡ በተጨማሪ ቀርቦላችኋልና፡ ተመልከቱት፡-

ይኸውም፡ የባዕዳኑን ሳይኾን፡ ከጥንቱ ጀምሮ፡ በእናንተው፡ በልጆቼ ዘንድ ተጠብቆ የኖረውን እግዚአብሔራዊ እውቀት የሚያሳየው፡ ኢትዮጵያዊው ይትበሃል ሲኾን፡ እርሱም፡ አንዱ ልጇና አገልጋዬ፡ ገዳማዊ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፡ በመንፈስ ቅዱስ በደረሰው፡ የመጽሓፈ ሰዓታቱ፡ ስብሓተ ፍቍር እና "ኵሎሙ" በሚል ርእስ በሚታወቀው፡ ብቸኛ የምስጋና ዝማሬው መካከል፡ በተለይ፡ "ዘእግዝእትነ ማርያም" በሚለው መግቢያና አዝማች ውስጥ ያለው፡ እንዲህ የሚለው ነው፡-

-"ኵሎሙ ሠራዊተ መላእክት፡ ይሴብሑኪ፤ <u>ዘእምቅድመ ዓለም፡ ሀልዎትኪ፤</u> ለማኅደረ ወልዱ፡ እግዚአብሔር ኀረየኪ።"

"የመላእክት ሠራዊት፡ <u>ከፍጥረተ ዓለም በፊት፡ የነበርሽበትን አኗኗርሽን እያዘከሩ፥</u> የልጁ ማደሪያ (እናት) ትኾኚ ዘንድ፡ እግዚአብሔር ስለመረጠሽ፡ እያደነቁም፡ ኹሉም ያመሰግኑሻል።"

-"ቅድስት፡ ቅድስት፡ ቅድስት ማርያም፡ መንበረ ጸባዖት ዘአርያም፤ቤዛዊተ ኵሉ ዓለም።"

"በሰማያት፡ የሥላሴ ዙፋን፥ ለዓለሙም ኹሉ፡ ቤዛ የኾንሽ' ቅድስት፡ ቅድስት፡ ቅድስት ማርያም፡ አንቺ ነሽ!"

-"እምቅድመ ሰማያት ወምድር ሀልዎትኪ፤ ፀሓይ ወወርኀ ኢቀደሙኪ፤ መላእክተ ሰማይ ይትለአኩኪ።"

"ከሰማይና ከምድር መፈጠር አስቀድሞ ነበርሽ፤ ፀሓይና ጨረቃም በፍጥረታቸው፡አልቀደሙሽም፤ የሰማይ መላእክትም፡ ምንጊዜም ያገለግሉሻል።"

\+ \+ \+

**ተዐውደ፡ በሚያዝያ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።**

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።